# ከአንድ ሺ ዓመት በፊት

የዛሬ አንድ ሺ ዓመት በፊት ኢትዮጵያ ትተዳደር የነበረዉ **በዛግዌ ሥርወ መንግሥት** ነበር። በግዕዝ ዛግዌ ማለት « የ **አገዉ** » ማለት ሲሆን ዘመነ መንግሥቱም የዛግዌ (የአገዉ) ሥርወ መንግሥት ይባል ነበር። በወቅቱ ግእዝ በቤተ ክህነትም ሆነ በቤተ መንግሥት ደረጃ ብሔራዊ የመግባቢያ ቋንቋ ነበረ። የዛግዌ ሥርወ መንግሥት የጀመረዉ ከዮዲት ጉዲት ( እሳቶ ) ወረራ በኋላ በ922 ዓ.ም ሲሆን ያበቃዉ ደግሞ በአጼ ይኩኖ አምላክ ዘመነ ንግሥና በ 1270 ዓ.ም ነዉ።

የመጀመሪያዉ የዛግዌ ንጉሥ **መራ ተክለ ሃይማኖት** ይባላል። **መራ** ከክርስቲያን ልዑላን አገዉ ቤተሰብ የተወለደ ላስቴ ነዉ። **መራ** የአጼ ድል ናዖድ (የአክሱም ዘመነ መንግሥት የመጨረሻዉ ንጉሥ) የጦር አዛዥ የነበረ ሲሆን ልጃቸዉን መሶበ ወርቅን ካገባ በኋላ አማቹን ገልብጦ የአዲሱ ሥርወ መንግሥት (የዛግዌ) መሥራች ለመሆን በቅቷል።

ኩሻዊና ሴማዊ ቋንቋዎችን የሚናገሩት አገዎች በኢትዮጵያ የመጀመሪያዎቹ ሰፋሪዎች ወይም ቀደምት ኗሪዎች መሆናቸዉን ኤድዋርድ አሌንዶርፍ ፣ ፣ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፣ ታደሰ ታምራት እና ሌሎችም በርካታ ታሪክ ጸሐፊዎች ይስማማሉ። በጊዜዉ ከተከዜ ወንዝ በስተምሥራቅ እና ከሰሜን ተራራ በስተደቡብ ጣና ሐይቅ አካባቢ **አገዉ ምድር** በመባል ይታወቅ የነበረ ሲሆን አገዎች በሚከተሉት አራት የኢትዮጵያ ክፍሎች ሰፍረዉ ይኖሩ እንደነበርም ይነገራል ።

- ካሚር የተባሉት ወሎ ዉስጥ ዋግ ሰቆጣና ላስታ ዳሞት አካባቢ ።
- ቅማንት የተባሉት ቤጌምድር ዉስጥ ቋራ አካባቢ።
- አዊ የተባሉት ጎጃም ዉሥጥ በጣና ሐይቅ በስተደቡብ በኩል ዳንግላና እንጂባራ አካባቢ።
- ቢለን የተባሉት ኤርትራ ዉስጥ ከረንና ሐማሴን አካባቢ መኖራቸዉ ይታወቃል።

ቤተ እሥራኤል (ፈላሻ) የተባሉትም የአገዉ ትዉልድ መሆናቸዉና በተለይ ቅማንትና ቋራ አካባቢ ጎንደር ይኖሩ የነበሩት በሙሉ የኋላ ኋላ ፈላሻ ተብለዉ በወታደራዊዎቹ ደርግና የኢህአዴግ መንግሥታት ትብብር ወደ እሥራኤል አገር እንዲፈልሱ መደረጋቸዉ ይታወቃል።

በዘመነ ዛግዌ በኢትዮጵያ ከተከናወኑት ተግባራት በዋነኛ ነት ተደጋግሞ የሚጠቀሰዉ **በገብረ መስቀል ላሊበላ** ጊዜ በ(1150 ዓ.ም. ገደማ) የታነጹት ታሪካዊዎቹ አሥራ አንዱ ዉቅር አብያተ ክርስቲያናት ሲሆኑ ከአንድ ዓለት ድንጋይ ተፈልፍለዉ የተሠሩ እጹብ ድንቅ አብያተ ክርስቲያናት መሆናቸዉን እና በቅዱሳን መላዕክት እርዳታ ጭምር በአጭር ጊዜ መፈጸማቸዉን **ገድለ ላሊበላ** ያስረዳል ።

**ላሊበላ** ወይም **ላል ይበላ** የሚለዉ አገዉኛ ቃል ወደ አማርኛ ሲተረጎም «ንቦች ግዛቱን ያዉቃሉ» እንደ ማለት

ሲሆን በዛግዌ ዘመነ መንግሥት ከነገሡት ነገሥታት መካከል ለ40 ዓመታት የነገሠዉ ነዉ:: **ላሊበላ** በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በኩልም ጻድቅ ሆኖ የተቆጠረ ታላቅና ቅዱስ ንጉሥ ነበር:: **ላሊበላ** ቡግና አካባቢ ቀድሞ ሮሃ በኋላም በእርሱ ስም ለመታሰቢያዉ « ላሊበላ » ተብሎ በተሰዬመዉ ቦታ **ጃን ስዩምና መስቀል ክብራ** ከተባሉት ወላጆቹ የተወለደ የቅዱስ ሐርቤ ወንድም ነዉ ። በጊዜዉ ቅድስት አገር ኢዬሩሳሌም በቱርክ እስላሞች ተወርራ ስለነበር በኢዬሩሳሌም ምትክ ኢትዮጵያን ዳግማዊት ኢየሩሳሌም ለማድረግ ተነሳስቶ ዉቅር አብያተ ክርስቲያናትን አንፇል:: መናገሻ ከተማዉ አቅራቢያ የሚገኙ በርካታ ቦታዎችንም ኢዬሩሳሌም ባሉ የአካባቢ ስሞች ሰይሟል:: ዘመነ ዛግዌን ከቀድሞዎቹ **አክሱማዉያን ነገሥታትም** ሆነ ከኋላዎቹ **ሰሎሞናዉያን ነገሥታት** ልዩ የሚያደርገዉ፦

- ልጅ አባቱን ሳይሆን ወንድም ወንድሙን ወይም የእህቱንና የወንድሙን ልጅ በመተካት ይነግሥ የነበረበት ወቅት መሆኑ::
- ዘመኑ ፍጹም ሰላምና መረጋጋት የሰፈነበት ወቅት የነበረ መሆኑ::
- ቤተ ክህነትና ቤተ መንግሥት መቀራረብ ያሳዩ የነበረበት ብቻ ሳይሆን ፍጹም አንድነት ያላቸዉ ይመስል የነበረበት ወቅት መሆኑና ከዛግዌ ነገሥታት መካከል አብዛኞቹ ጻድቅ ተብለዉ የተመሰከረላቸዉ ቅዱሳን የሃይማኖት ሰዎች መሆናቸዉ::
- አሥራ አንዱ ዉቅር አብያተ ክርስቲያናት የታነጹትና ከተሜነት (urbanization) የተካሄደበት የሥልጣኔ በር ከፋች ዘመን መሆኑ:: በጊዜዉ ከዉቅር አብያተ ክርስቲያናት መታነጽ በተጨማሪ በዮዲት ጉዲት ዘመን (852 - 892 ዓ.ም.) የወደሙ በወሎ በትግራይ በቤገምድር በርካታ ገዳማትና አድባራት መልሰዉ የተቋቋሙበትና የክርስትና ሃይማኖት የተስፋፋበት ጊዜ ከመሆኑ በተጨማሪ፡ በተለያዩ ሥፍራዎች ማለፊያ የግንብ ሕንጻዎች የተሠሩበት፡ ጥንታዊ የሥልጣኔ ጮራ የፈነጠቀበት ወርቃማ ዘመን ነበር::
- በንግድ በኩልም አክሱማዉያን ነገሥታት **በአዱሊስና ዳህላክ** ወደቦች ይጠቀሙ እንደነበረዉ ሁሉ ሰሜን ዳርቻ ከቀይ ባህር እስከ ሕንድ ዉቂያኖስ ድረስ ይገዙ የነበሩት የዛግዌ ነገሥታትም **በዘይላና በርበራ** ወደቦች ይገለገሉ ነበር::
- አንጻራዊ በሆነ መልኩ መረጃዎች በስፋት ከሚገኙ በት ከንጉሥ ላሊበላ ዘመነ መንግሥት በስተቀር የሌሎቹን ዛግዌ ነገሥታት ዘመነ መንግሥታትና ያከናወኑትን ተግባር በተመለከተ ለምርምርና ጥናት የሚረዱ መዛግብት በስፋት የማይገኙበት ብዙም ያልተጠናና ያልታወቀ ዘመን

በመሆኑ ከኢትዮጵያ ታሪክ ዉስጥ አብዛኛዉ የዛግዌ ክፍለ ዘመን « **የጨለማዉ ዘመን** » በመባል ስለሚታወቅም ዘመኑ ከሌሎቹ ክፍለ ዘመናት ለዩት ያለ ነዉ::

- ከ10ኛዉ መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ማለትም ከሁለተኛዉ ምዕት ዓመት (ሚሌኒዬም) መግቢያ እስከ 13ኛዉ መቶ ክፍለ ዘመን መገባደጃ ድረስ በነበሩት ከ300 ዓመታት በላይ ኢትዮጵያን ካስተዳደሩት የዛግዌ ነገሥታት መካከል መራ ተክለ ሃይማኖት፣ ግርማ ስዩም፣ ጃን ስዩም፣ ይምርሃነ ክርስቶስ፣ ቅዱስ ሐርቤ (ገብረ ማርያም)፣ ላሊበላ፣ ታታዲዬም፣ ነአኵቶለአብ፣ ይትባረክ፣ እና ማይራሪ ይጠቀሳሉ::
- የዛግዌ ነገሥታት በቴክኒካዊ ጥበብና በዲፕሎማሲ ተልዕኮም ዉጤታማ እንደነበሩ የሚያመለክቱ የታሪክ ማስረጃዎች አሉ:: «ሰሎሞናዉያን አይደላችሁም» በማለት ለንግሥናቸዉ እዉቅና ላለመስጠት ያንገራግሩ ለነበሩት ግብጻዉያን ጳጳሳት በተለይም ከግብጽ የመጡት አቡነ ሀቢብ ተቃዉመዉ በነበረ ጊዜ፡ ትዉልደ ሙሴ እሥራኤላዉያን መሆናቸዉን በመግለጽ ነገሥታትነታቸዉን በዉድም ሆነ በግድ ለማሳመን መሞከራቸዉና ግብጽ አገር በተደጋጋሚ መልዕክተኛ በመላላክ ያላሰለሰ ዲሎማሲያዊ ጥረት አድርገዉ የካህናትን ይሁንታ ለማግኘት ነገሥታቱ ያደረጉት ብርቱ ጥረት ወይም የዉጭ ግንኙነት ተልዕኮ እዚህ ላይ እንደ ምሳሌ ሊጠቀስ ይችላል:: ዛግዌዎች በተለይ ወደ ኢየሩሳሌምና ግብጽ አገራት ለሃይማኖታዊ ጉዳይ በተደጋጋሚ የዉጭ ግንኙነት ተልዕኮ /ዲፕሎማሲያዊ ሥራ/ ይፈጽሙ እንደነበር በታሪክ ማኅደር ተዘግቧል ::

የጀመርነዉን እሥራ ምዕት ዓመት( ፳፻ ዓ.ም. ) ምክኒያት በማድረግ «**ከአንድ ሺ ዓመት በፊት**» በሚል ርዕስ ከሰፊዉ የዘመነ ዛግዌ ታሪክ ጨለፍ አድርገን ይህችን ታክል ካስቃኘናችሁ በወቅቱ ስለነበረዉ አጠቃላይ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ እና ሃይማኖታዊ ሁኔታ ዝርዝሩን ለመረዳት የታሪክ ማኅደራችንን ማገላበጥ ይበጃል:: ረዥሙን የአገራችንን ታሪክ ማኅደር ስናገላብጥ ከአንድ ሺ ዓመት በፊት ከዛግዌ ነገሥታት ታሪክ ጎን ለጎንም በምሥራቃዊዉ የኢትዮጵያ ክፍል **የሐረር ከተማን** መቆርቆርና የባህላችንን ሁለገብ እድገት መቃኘት እንችላለን:: ኢትዮጵያ የክርስቲያን ብቻ ሳይሆን የእስላምም አገር፡ የአንድ ብሔር ወይም ጎሳ ብቻ ሳይሆን የብሔር ብሔረሰብ አገር መሆኗንና እኒህም በሺህ ዓመታት ለሚቆጠሩ ዘመናት በወንድማማችነት ተከባብረዉና ተቻችለዉ የኖሩባት ታሪካዊት አኩሪ አገር መሆኗን ጭምር ልብ ይሏል::

መ/ር መስፍን ብርሃኑ
/B.Th., M.Phil., Th.M./ **ከቶሮንቶ**